የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

# የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድ ለማቋቋም

# እንደገና የወጣ መመሪያ 180/2013

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
መዝገብና ማህደር
Record and File
Ministry of Labour and Social Affairs

የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

# የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድ ለማቋቋም እንደገና የወጣ መመሪያ

1. አውጭው ባለሥልጣን፣

የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 171 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድ ለማቋቋም እንደገና ይህን መመሪያ አውጥቷል::

2. አጭር ርዕስ፣

ይህ መመሪያ "የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድ ለማቋቋም የወጣ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

3. ትርጓሜ፣

በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

1/ "የሥራ ሁኔታ" በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 2/6/ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል::

2/ "የኢትዮጵያ አሠሪዎች ፌዴሬሽን" ማለት በሕግ መሠረት በሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በሥራ ላይ የሚገኝ የኢትዮጵያ አሠሪዎች ማኅበር ነው::

3/ "የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን" ማለት በሕግ መሠረት በሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ተመዝግቦ የሚገኝ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ነው።

4/ "ሚኒስትር" ወይም "ሚኒስቴር" ማለት እንደአግባቡ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ወይም ሚኒስቴር ነው።

## 4. ስለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድ መቋቋም፣

1/ በዚህ መመሪያ መሠረት ቋሚ የሆነ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድ በሚኒስትሩ ይቋቋማል።

2/ ቦርዱ በሚኒስቴሩ መ/ቤት የሚደራጅ፣ የራሱ ኃላፊ ያለው፣ አስፈላጊ የሰው ኃይል እና በጀት የሚኖረው ጽ/ቤት ይኖረዋል።

## 5. የአማካሪ ቦርዱ ተግባርና ኃላፊነት፣

1/ ቦርዱ፣

ሀ. የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይን በሚመለከቱ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ላይ እንደአስፈላጊነቱ ሊደረግ ስለሚገባው ማሻሻያ፣ ማስተካከያ ወይም በአዲስ መልክ ሊወጡ ስለሚገባቸው ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች፣

ለ. የሥራ ሥምሪት የሚስፋፋበትንና የሥራ አጥነትን ደረጃ በደረጃ መቀነስ ስለሚቻልበት መንገድ፣

ሐ. አጠቃላይ የሥራ ሁኔታዎች ስለሚሻሻሉበት፣ የኢንዱስትሪ አደጋዎችና ያተለያዩ የሙያ ጠንቆች ስለሚወገዱበት እንዲሁም የሠራተኛው ማኅበራዊ ኑሮ ሊዳብር ስለሚችልበት ሁኔታ፣

የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

# የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድ ለማቋቋም እንደገና የወጣ መመሪያ /ረቂቅ/

1. ## አውጭው ባለሥልጣን፣

የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 171 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድ ለማቋቋም እንደገና ይህን መመሪያ አውጥቷል።

2. ## አጭር ርዕስ፣

ይህ መመሪያ "የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድ ለማቋቋም የወጣ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

3. ## ትርጓሜ፣

በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

1/ "የሥራ ሁኔታ" በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 2/6/ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል።

2/ "የኢትዮጵያ አሠሪዎች ፌዴሬሽን" ማለት በሕግ መሠረት በሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በሥራ ላይ የሚገኝ የኢትዮጵያ አሠሪዎች ማኅበር ነው።

7. <u>የመተባበር ግዴታ፣</u>

ማንኛውም ጉዳዩ የሚመከለተው መ/ቤት ወይም ግለሰብ ይህ መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን የመተባበር ግዴታ አበለት::

8. <u>የተሻረ መመሪያ፣</u>

የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድ ለማቋቋም ግንቦት 15 ቀን 1987 የወጣው መመሪያ ተሽሯል::

9. <u>መመሪያው ስለሚጸናበት ጊዜ፣</u>

ይህ መመሪያ ከ 17 ጥቅም 1991 ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ሀሰን አብደላ

የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ✦ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር